OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# የCityArtist የ2024 መመሪያዎች

## *የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ አጠቃላይ እይታ*

የCityArtist (የከተማ አርቲስት) የድጋፍ ስጦታ ፕሮግራም ሲያትልን መሰረት ላደረጉ በፈጠራ ስራ ውስጥ ምርምር፣ ዕድገት/ ልማት፣ እና የፈጠራ ችሎታ አቅርቦት ለሚያደርጉ አርቲስቶች/ የሙዚየም ኃላፊ ግለሰቦችን ይደግፋል። የ2024 ማመልከቻ **ለሥነ ጽሑፍ፣ ለሚዲያ/ ለዲጂታል/ ለፊልም** (**የስክሪን ጽሑፍን** ጨምሮ)፣ እና ለ **ምስላዊ** ጥበብ ክፍት ነው። የድጋፍ ስጦታውን የተሸለሙ አርቲስቶች በሲያትል ከተማ ክልሎች ውስጥ ለህዝብ አቅርቦት ማድረግ አለባቸው።

CityArtist በባህላዊው ዘርፍ እምብርት የሆኑትን አርቲስቶችን፣ አድራጊዎችን/ሰሪዎች፣ እና የሙዚየም ኃላፊዎችን እየደገፈ ያቆያል። ለፈጠራ ስራ ፈጣሪዎች የገንዘብ ድጋፍ መስጠት በከተማው ሁሉ ውስጥ ላሉ ሰፈሮች ሰፊ ኢኮኖሚ እና የህይወት ጥራት አስተዋፅኦ ያደርጋል።

**ለማመልከቻው መረጃ እና እገዛ፣ ለብቁነት ወይም በመስመር ላይ የቴክኒክ ድጋፍ:** የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ አይሪን ጎሜዝን (Irene Gómez) በ (206) 684-7310 **ወይም** irene.gomez@seattle.gov **ያግኙ**።

| | |
|---|---|
| **ማመልከቻ**<br>ማመልከቻው በመስመር ላይ (ONLINE) ይገባል።<br>ማመልከቻው በFLUXX ላይ በሲያትል ከተማ የድጋፍ ስጦታ ድህር መግቢያ በኩል https://seattle.fluxx.io/user_sessions/new ላይ ይገኛል<br><br>ኮምፒውተር ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት መዳረሻ ከሌለዎት፣ ሰራተኞችን በተቻለ ፍጥነት ያግኙ። | **የሚከፈተው**<br>መጋቢት 28 ቀን 2023 - ጥዋት 8 ሰዓት (ፓስፊክ)<br><br>**የሚያበቃበት**<br>ግንቦት 9 ቀን 2023 - ከምሽቱ 5 ሰዓት (ፓስፊክ) |
| **የመረጃ ክፍለ-ጊዜዎች:**<br>**አውደ ጥናት 1**<br>ማክሰኞ፣ ሚያዝያ 11፣ ከጥዋት 11:30 - ከሰዓት 1:30 (ፓስፊክ)<br>መልስ ይስጡ<br><br>**አውደ ጥናት 2**<br>ማክሰኞ፣ ሚያዝያ 18 ቀን፣ ከምሽቱ 3 ሰዓት- ምሽቱ 5 ሰዓት (ፓስፊክ)<br>መልስ ይስጡ | **የማመልከቻ ረቂቅ ግምገማ ክፍለ ጊዜዎች:**<br>**የረቂቅ ግምገማ 1**<br>ማክሰኞ፣ ሚያዝያ 25፣ ከሰዓት በኋላ ከ1 - 5 ሰዓት (ፓስፊክ)<br>መልስ ይስጡ<br><br>**የረቂቅ ግምገማ 2**<br>ማክሰኞ፣ ግንቦት 2፣ ከሰዓት በኋላ ከ1 - 5 ሰዓት (ፓስፊክ)<br>መልስ ይስጡ |

**በስራ ሰዓቶች ስልክ ይደውሉ**
ረቡዕ፣ መጋቢት 29 - ግንቦት 3፣ ከሰዓት በኋላ ከ3 - 5
ሰዓት (ፓስፊክ)

## *<u>የገንዘብ ድጋፍ</u>*

ከሶስቱ መጠኖች: $2,000፣ $5,000 ወይም $8,000። <u>አንዱን ይመርጣሉ</u>

## *<u>የብቁነት/ መስፈርቶች</u>*

እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ ለዚህ የድጋፍ ስጦታ ብቁ ነዎት:

- የጥበብ ሥራ የሚያመርት/ የሚያቀርብ ማፍራት የሚችል አርቲስት/ የሙዚየም ኃላፊ፤
- እርስዎ አንድ የሲያትል ነዋሪ ነዎት ወይም ደብዳቤ በሚቀበሉበት በሲያትል ከተማ ገደቦች ውስጥ ቋሚ ስቱዲዮ/ የስራ ቦታ በስምዎ ያለዎት። የፖስታ ሳጥን * ሊሆን አይችልም፤
- በማመልከቻው የቀነ ገደብ ማብቂያ ቀን ቢያንስ የ18 ዓመት ዕድሜ የሆኑ፤
- እርስዎ የመጀመሪያ ዋናውን ይዘት የሚፈጥር ግለሰብ አርቲስት/ የሙዚየም ኃላፊ ነዎት ወይም እርስዎ የአርቲስቶች/ተቆጣጣሪዎች ቡድን መሪ አርቲስት/ የሙዚየም ኃላፊ ነዎት
  - አመልካቹ የኪነጥበብ ወይም የባህል ቡድን/ ድርጅት መሪ አርቲስት/ የሙዚየም ኃላፊ ከሆነ
- ይህንን የድጋፍ ስጦታ ሽልማት ስራ ከድርጅቱ ቀጣይ/ ወቅታዊ ስራ በግልፅ መለየት ይችላሉ።

ለዚህ የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ ብቁ የማይሆኑ:

- ከሥነ ጥበባዊ ሥራዎ ወይም ከሙያዎ ጋር በተዛመደ በማንኛውም የዲግሪ መርሃ ግብር ትምህርት ቤት (ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ የምሩቅ፣ ወይም የዶክትሬት) ተመዝግበው ከሆነ።
- እርስዎ አሁን የሚሰራ ንቁ ውል ካለው ከሌላው የኛ ፕሮግራም የአሁኑ የድጋፍ ስጦታ ሽልማት ተቀባይ ከሆኑ።

## *<u>የግምገማ መስፈርቶች</u>*

የሚቀርቡ የውሳኔ ሃሳቦች ሶስት (3) መመዘኛዎችን መሰረት በማድረግ ይገመገማሉ። በእርስዎ ማመልከቻ መረጃዎች/ ይዘቶች ውስጥ ለነዚህ መመዘኛዎች ምላሽ እንዲሰጡ እናበረታታዎታለን። እያንዳንዱ ከዚህ በታች ያለው መስፈርት **በእኩል ዋጋ** በድምሩ 60 ነጥቦች ይገመገማል።

### ልምድ እና እምቅ ችሎታ (20 ነጥቦች)

- ስራዎን የሚያነቃቃ፣ ተፅዕኖ የሚያመጣ ወይም የሚቀርጸውን እና/ወይም በተግባርዎ/ በተሞክሮዎ ላይ ለውጦችን ስለሚያነሳሱ ያጋሩ።

- እንደ አርቲስት ወይም የሙዚየም ኃላፊ የእርስዎን የልምድ፣ የስልጠና፣ ያለፈ ታሪክ ወይም ስራ ዓይነቶች ይግለጹ።

**የኪነ ጥበባዊ እድገት እና ራዕይ (20 ነጥቦች)**

- በጊዜ ሂደት መለኪያ፣ ልኬትዎን፣ ጭብጥዎን፣ ወይም ቴክኒክዎን በግልፅ ያስተላልፉ። ምን ምን መዝለሎች/ እልፍቶች ወይም አሰሳዎች እንደተወሰዱ ወይም በቀጣይ እንደሚወሰዱ ያመልክቱ።

**የሥራ አካል (20 ነጥቦች)**

- የእርስዎ ስራ ናሙናዎች የትረካ ምላሾችን፣ የዕደ ጥበብ ደረጃን ወይም የሚቀጥለውን ማለፊያ እንዴት እንደሚያንጸባርቁ ያሳዩ። የእርስዎ የስራ ናሙናዎች የሚነበቡ፣ የሚሰሙ እና/ወይም በትኩረት/የሚታዩ ናቸው።

## *<u>የማመልከቻ አጭር መግለጫ እና አካላት</u>*

ማመልከቻው ያተኮረው በእርስዎ የአርቲስት ተሞክሮ፣ ሃሳቦች፣ እና በጊዜ ሂደት እድገት ላይ ነው። ሶስት ዋና የማመልከቻ አካላት የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- እርስዎ እና የእርስዎ ስራ በጊዜ ሂደት እንዴት እንደዳበራችሁ የሚናገሩ <u>ሁለት የትረካ ጥያቄዎች</u>።
- ስልጠናዎችን፣ ክስተቶችን፣ ማስተማርን/ ሌክቸሮችን፣ ችሎታዎችን ከድርጅቶች ጋር በመተባበር ማሳየት፣ መጣጥፎችን፣ ወዘተ የሚያካትት የስኬቶች ታሪክዎን የሚዘረዝር <u>የትምህርት እና ሥራዎች ታሪክ ዝርዝር ጽሁፍ</u>።
- <u>የሥራ ናሙና(ዎች)</u> የትረካ ምላሾችን የሚደግፍ እና የትምህርት እና ሥራዎች ታሪክ ዝርዝር ጽሁፍ።